# ሙሐመድ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሶአልን?




አንድ፤

የሙሴ ወንድም ሙሐመድ

ሙስሊሞች የኢስላም ነቢይ ሙሐመድ በተውራት ወይም ኦሪት እና ኢንጅል ወይም ወንጌል፥ ማለትም በአይሁድ እና በክርስቲያኖች መጽሐፍ በብሉይ እና አዲስ ኪዳን ተደጋግሞ እንደተጻፈና እንደተተነበየ ይናገራሉ። ይህን የሚሉት በሱራ 61፥6 ዒሳ ከእርሱ በኋላ አሕመድ የተባለ መልእክተኛ እንደሚመጣ ስለ ተናገረ ነው። ጥቅሱ እንዲህ ይላል፤

የመርየም ልጅ ዒሳም፡- «የእስራኤል ልጆች ሆይ! እኔ ከተውራት በፊቴ ያለውን የማረጋግጥና ከእኔ በኋላ በሚመጣው መልክተኛ ስሙ አሕመድ በኾነው የማበስር ስኾን ወደእናንተ (የተላክሁ) የአላህ መልክተኛ ነኝ» ባለ ጊዜ (አስታውስ)፡፡ በግልጽ ተዓምራቶች በመጣቸውም ጊዜ «ይህ ግልጽ ድግምት ነው» አሉ፡፡ ይላል።

ዒሳ ለሙስሊሞች እንደሚመስላቸው ኢየሱስ ነው። ነገር ግን ዒሳና ኢየሱስ ከቶም አንድ አይደሉም። ይህ ራሱን የቻለ ጉዳይ ነውና እንለፈው። በነገራችን ላይ እንደዚህ የሚሉት እንደ አሕመድ ዲዳት እና ዛኪር ናይክ የመሰሉት ስለ መጽሐፍ ቅዱስ እናውቃለን የሚሉ ናቸው እንጂ የቀደሙት ሙፈሲሮች ይህንን አላሉም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሙሐመድ ተተንብዮአል የሚሉት ደግሞ የአይሁድም የክርስቲያኖችም መጽሐፎች የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዟል እያሉም ነው። ይህ የመበረዝ ጉዳይም

ራሱን የቻለ ሌላ ርእስ ነውና እንለፈው። እና ይህ የተበረዘ የሚሉት መጽሐፍ ስለ ሙሐመድ ተነበየ የሚሉትን ወይም እንደተነበየ የሚመስላቸውን ምንባቦች መበረዙንና መበላሸቱን ሳይጠራጠሩ ይቀበሉታል።

እነዚህን ሙሐመድ ተጠቀሰባቸው የሚሏቸው ምንባቦች ብዙ አይደሉምና እንመለከታቸዋለን። በእውነት ስለ ሙሐመድ እንደሚናገሩም እንፈትሻቸዋለን። ባለፈው፥ 'አጽናኙ ሙሐመድ' በሚል በዮሐንስ ወንጌል ከ14-16 ባሉት ምዕራፎች ስለ አጽናኙ (ጰራቅሊጦስ ወይም መንፈስ ቅዱስ) የተነገረው ስለ ሙሐመድ የተተነበየ ትንቢት ነው ስለሚሉት ተመልክተናል። ቀጥሎ በዚህ ክፍል ደግሞ ከሙሴ በኋላ የሚመጣው ነቢይ የተባለው ሙሐመድ ነው የሚሉትን እንመለከታለን።

የተነገረው ትንቢት እንዲህ የሚል ነው፤ ዘዳ. 18፥18-19 ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ፥ ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል፤ በስሜም የሚናገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀልለታለሁ።

ይህ ክፍል ሙስሊሞች ስለ ሙሐመድ የተተነበየ ትንቢት ነው ብለው የሚያሸበርቁት ምንባብ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዟል እያሉ ይህ ክፍል አልተበረዘም የሚሉ ከሆነ መጽሐፉን ወይም የጥቅሱን ዙሪያ ገባ (ዐውድ) ይቀበላሉ ማለት ነው። እዚያው 18፥16 ላይ፥ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል፤ እርሱንም ታደምጣለህ። የሚል ቃል አለ። እነዚህ ጥቅሶች

ሙስሊሞች ሙሴና ሙሐመድ የሚገናኙባቸው መመሳሰሎች በማለት የሚዘረዝሯቸው ነገሮች አሉ፤ ሙሴ የሕዝቡ መሪ፥ ሙሐመድም የሕዝቡ መሪ፤ ሙሴ ሕግ የሰጠ፥ ሙሐመድም ሕግ የሰጠ፤ ሙሴና ሙሐመድ እናትና አባት አላቸው፤ ወዘተ፥ ይላሉ። ይህንን፥ 'እናትና አባት አላቸው' የሚሉት ያ ነቢይ ኢየሱስ እንዳልሆነ ከንጽጽሩ ውስጥ ለማውጣት ነው። በዚህ መልኩ ከዘረዘርን፥ ማለቂያም የለውም፤ ማንንም ከማንም ጋር ልናመሳስልም እንችላለን። ሙሴም ሙሐመድም በ'ሙ' ይጀምራሉ፤ ሁለቱም አሥር ጣቶች አሏቸው፤ ወዘተ ማለትም እንችላለን። እንደዚያ የመሰሉ ዝርዝሮች የሚያቀርቡም አሉ።

እዚህ እግዚአብሔር የተናገረው ለእስራኤል የሚሰጣቸው፥ 'እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ' በእውነት የኢስላም ነቢይ ሙሐመድ ነው? ሙሐመድ በእውን የእስራኤል ልጆች ወንድም ነው? 'ወንድም ሲባል ሰፊ ትርጉም አለውና የእስማኤል ልጅ ያው የአብርሃም ልጅ መሆኑ ነው።' ይላሉ። ሲጀመር ሙሐመድ የእስማኤል ልጅ ስለመሆኑ ማረጋገጫ የለም። ሙሐመድ ዓረባዊ ነው። ዓረባውያን የምድረ በዳ ሰዎች ማለት ነው እንጂ አንድ ወይም ሌላ ጎሳም አይደለም። ከእስማኤል 12 ነገዶች ውስጥ ደግሞ ዓረባውያን የሉም። ደህና፤ ከነዚያ አንዱ ናቸው ብለን እንውሰድ። ከሆነም እስማኤል ራሱ ግማሽ

ዕብራዊ ግማሽ ግብፃዊ መሆኑን መርሳት የለብንም። ተጨባጭ ማረጋገጫ ባይኖርም፥ 'ይሁን፤ እስማኤላዊ ነው።' ብለን እንውሰድ።

እዚህ እግዚአብሔር እየተናገራቸው ያለው ግን ለእስማኤል ልጆች ሳይሆን ለይስሐቅ ልጆች ነው። ከይስሐቅ እና ከእስማኤልም ሌላ አብርሃም ብዙ ልጆች ነበሩትና እዚህ የተነገረው ይስሐቅ መሆኑ ይሰመርበት። ከይስሐቅም ደግሞ የዔሳው ሳይሆኑ የያዕቆብ ልጆች ናቸው እዚህ ይህ፥ 'ከወንድሞቻችሁ መካከል' የሚለው ቃል የተነገራቸው። ከእስማኤል ይልቅ ዔሳው ወይም ኤዶማውያን ለእስራኤል ይቀርባሉ። እንዲያውም የዔሳው ልጆች፥ 'ወንድሞቻችሁ' ተብለዋል፤ ዘዳ. 2፥4። እንዲያም ሆኖ ይህ እዚህ የምንመለከተው ቃል እነሱን እንኳ አይመለከትም።

ከወንድሞቻቸው መካከል የሚል ሌላ አሳብ ብንወስድ ይህንን አሳብ ይበልጥ ይከስትልናልና ያንን እንይ። በዘዳ. 17፥15 ላይ፥ አምላክህ እግዚአብሔር የመረጠውን በላይህ ታነግሣለህ፤ ከወንድሞችህ መካከል የሆነውን በአንተ ላይ ንጉሥ ታነግሣለህ፤ ወንድምህ ያልሆነውን ከሌላ ወገን ሰው በላይህ ንጉሥ ታደርግ ዘንድ አይገባህም። የሚል ቃል ይገኛል። እስራኤል ወደፊት ንጉሥ እንደሚያነግሡ ተነገራቸው፤ ደግሞም አነገሡ። እና ያነገሡት ከማን ወገን ነው? ከእስማኤላውያን ወይም ከኤዶማውያን ሊያነግሡ ከቶስ ይታሰባልን? አይታሰብም። በእስራኤል ላይ የነገሡት የመጀመሪያዎቹ ንጉሦች ሳኦል፥ ዳዊት፥ እና ሰሎሞን ከየት ናቸው? ከእስራኤል። ከዳዊት በኋላ ሁሉም ከይሁዳ ነገድ ናቸው። ከዚያ በኋላ እሁለት ተከፍለው የሰሜኑ የተለያዩ ሰዎች ቢነግሡባቸውም በደቡቡ ሁሉም የሰሎሞን ዘር ልጆች ናቸው። በሰሜኑም የነገሡት ጥቂት ቅይጦች ቢኖሩም አይሁዳውያን ናቸው። ነገሥታቱም፥ ነቢያቱም እንደሚነሡ የተነገረባቸው ወንድሞች በእርግጥ ወንድሞቻቸው የሆኑ የእስራኤል (ያዕቆብ) ልጆች እንጂ ሌላ አይደሉም። በሕጋዊነት የነገሡት ነገሥታት ሁሉ አይሁዳውያን ብቻ ናቸው። ስለ ነቢዩ፥ 'ወንድም' የሚለው ቃልና ስለ ንጉሦቻቸው፥ 'ወንድም' የሚለው ቃል ተመሳሳይ ሆኖ፥ ቃሉ ብቻ ሳይሆን አሳቡም ተመሳሳይ ነው።

ደግሞም ያ ነቢይ ለማም ነው የሚነሣው? ወይም እግዚአብሔር ለማን ነው የሚያስነሣላቸው? ለእስራኤላውያን። ሙሐመድ የአይሁድ ወይም የእስራኤላውያን ነቢይ አይደለም። ሙሐመድ የመካና አካባቢዋ አስፈራሪ ተደርጎ የተላከ እንጂ ለአይሁድ የተላከ አይደለም። 'የለም፤ እርሱ ለዓለሙ ሁሉ የተላከ ነው' ከተባለም አለመሆኑን የሚያረጋግጠው የተወረደለት በዐረብኛ ብቻ መሆኑ ነው። ቁርአን 42፥7 እንደዚሁም የከተሞች እናት የሆነችውን (የመካን ሰዎች)፣ በአካባቢዋ ያሉትንም ልታስፈራራ፣ የመሰብሰቢያውንም ቀን፣ በርሱ ጥርጣሬ የሌለበት ሲሆን ልታስጠነቅቅ ዐረብኛ የሆነን ቁርአን ወደአንተ አወረድን፤ (ከነሱም) ከፊሉ በገነት ውስጥ ከፊሉም በእሳት ውስጥ ነው። ይላል። በተጨማሪ፥ 16፥103፤ 20፥113፤ 41፥3፤ 43፥3፤ 46፥12፤ ወዘተ፥ ቁር ኣን የተወረደው በዐረብኛ መሆኑ ለዐረብኛ ተናጋሪዎች መሆኑን ያሳያል። አይሁድ ደግሞ ዐረብኛ ተናጋሪ አይደሉም። ሙሐመድ የተነሣውም ለአይሁድ እና በአይሁድ መካከል አይደለም።

ታዲያ ይህ ከወንድሞቻቸው መካከል የሚነሣ ነቢይ ማን ነው? በአዲስ ኪዳን ይህ ነቢይ ማን መሆኑ በእርግጥና በግልጽ ተጽፎአል። በሐዋርያት ሥራ ይህ የዘዳግም ጥቅስ ሁለቴ የተጠቀሰ ሲሆን (ሐዋ. 3፥22 እና 7፥37) ከሁለቱ በአንዱ በእርግጥ ያ ነቢይ ኢየሱስ መሆኑ በግልጽ ተጽፎአል። ቃሉ የራሱ ምስክር ነውና ቃሉ የሚለውን እናንብብ፤ ሐዋ. 3፥13-26 ይህን ይላል፤

የአብርሃምና የይስሐቅ የያዕቆብም አምላክ፥ የአባቶቻችን አምላክ፥ እናንተ አሳልፋችሁ የሰጣችሁትንና ሊፈታው ቈርጦ ሳለ በጲላጦስ ፊት የካዳችሁትን ብላቴናውን ኢየሱስን አከበረው። እናንተ ግን ቅዱሱን ጻድቁንም ክዳችሁ ነፍሰ ገዳዩን ሰው ይሰጣችሁ ዘንድ ለመናችሁ፥ የሕይወትንም ራስ ገደላችሁት፤ እርሱን ግን እግዚአብሔር ከሙታን አስነሣው፥ ለዚህም ነገር እኛ ምስክሮች ነን። በስሙም በማመን ይህን የምታዩትንና የምታውቁትን የእርሱ ስም አጸናው፥ በእርሱም በኩል የሆነው እምነት በሁላችሁ ፊት ይህን ፍጹም ጤና ሰጠው። አሁንም፥ ወንድሞቼ ሆይ፥ እናንተ እንደ አለቆቻችሁ ደግሞ ባለማወቅ እንዳደረጋችሁት አውቄአለሁ፤ እግዚአብሔር ግን ክርስቶስ መከራ እንዲቀበል አስቀድሞ በነቢያት ሁሉ አፍ የተናገረውን እንዲሁ ፈጸመው።

እንግዲህ ከጌታ ፊት የመጽናናት ዘመን እንድትመጣላችሁ አስቀድሞም ለእናንተ የመረጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲልክላችሁ፥ ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ ተመለሱም። እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በቅዱሳን ነቢያቱ አፍ የተናገረው፥ ነገር ሁሉ እስከሚታደስበት ዘመን ድረስ ሰማይ ይቀበለው ዘንድ ይገባልና። ሙሴም ለአባቶች፡- ጌታ አምላክ እኔን እንዳስነሣኝ ነቢይን ከወንድሞቻችሁ ያስነሣላችኋል፤ በሚነግራችሁ ሁሉ እርሱን ስሙት። ያንም ነቢይ የማትሰማው ነፍስ ሁሉ ከሕዝብ ተለይታ ትጠፋለች አለ። ሁለተኛም ከሳሙኤል ጀምሮ ከእርሱም በኋላ የተናገሩት ነቢያት ሁሉ ደግሞ ስለዚህ ወራት ተናገሩ። እናንተ የነቢያት ልጆችና እግዚአብሔር ለአብርሃም፡- በዘርህ የምድር ወገኖች ሁሉ ይባረካሉ ብሎ፥ ከአባቶቻችን ጋር ያደረገው የኪዳን ልጆች ናችሁ። ለእናንተ አስቀድሞ እግዚአብሔር ብላቴናውን አስነሥቶ፥ እያንዳንዳችሁን ከክፋታችሁ እየመለሰ ይባርካችሁ ዘንድ፥ ሰደደው።

ያ ከወንድሞቻችሁ መካከል የተባለው ነቢይ ሌላ ማንም ሳይሆን ኢየሱስ ነው።




ሁለት፤

አጽናኙ ሙሐመድ

ከዮሐ. 14-16 የተጻፈውን #አጽናኙ ሙስሊሞች ሙሐመድ ነው እንደሚሉ እናውቃለን?

በሱራ 61፥6 እንዲህ የሚል ጥቅስ አለ፤ የመርየም ልጅ ዒሳም፥ የእስራኤል ልጆች ሆይ እኔ ከተውራት በፊቴ ያለውን የማረጋግጥና ከኔ በኋላ በሚመጣው መልክተኛ ስሙ አሕመድ በሆነው የማበስር ስሆን ወደናንተ (የተላክሁ) የአላህ መልክተኛ ነኝ ባለ ጊዜ (አስታውስ)፤ በግልጽ ታምራቶች በመጣቸውም ጊዜ ይህ ግልጽ ድግምት ነው አሉ።

ስሙ አሕመድ የሆነውን አብሳሪው የመርየም ልጅ ዒሳ ነው። ዒሳና ኢየሱስ የተለያዩ መሆናቸውን ወይም የቁርኣኑ ዒሳ የመጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስ አለመሆኑን ደጋግሜ ጽፌአለሁ። መጽሐፍም ሳይቀር ጽፌበታለሁ። ለጊዜው ግን ለእነርሱ እንደመሰላቸው ወይም እንደነሱ እናስብና ዒሳ ኢየሱስ ነው እንበል።

ችግሩ የሚፈጠረው ዒሳ ስለ አሕመድ የተናገረው መቼ ነው? ቢባል ያንን የሚመስል ነገር የለም። ከየት ይምጣ? ከየትም። አሕመድ ዲዳት ቢቸግረው ከእርሱ በፊት ከጻፈ

አንድ ሰው ወስዶ፥ አጽናኝ (ጰራቅሊጦስ) የሚለውን በግሪክ παράκλητος (ፓራክሌቶስ) የሚባለውን፥ እርሱ ግን περικλυτος ፔሪክሉቶስ ነው፤ ትርጉሙም ከአሕመድ ይመሳሰላል ብሎ ተናገረም፤ ጻፈም።

ይህንን የዮሐንስ ወንጌል ክፍል ፔሪክሉቶስ በሚል ቃል የጻፈ አንድም ሰነድ፥ አንድም ትርጉም ግን ኖሮ አያውቅም። ያው ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዟል፥ ተደልዟል፥ ተከልሷል ስለሚሉና፥ (በነገራችን ላይ ይህንን ቃል የኢስላም ነቢይ ሙሐመድም እንኳ አላለም።) ይህንን የተደለዘውንና የተበረዘውን እንድናስተያይ ያልተበረዘውን አምጡ ሲባል ሊያመጡ ስለማይችሉ እንደተበረዘ እንቁጠርና ይህ አጽናኝ ሙሐመድ ነው እንበል።

እንግዲህ አጽናኙ ሙሐመድ ከሆነ፥ ይህንን የሚሉ ሙስሊሞች ሊወጡ የማይችሉት ገደል ውስጥ ራሳቸውን ይከትታሉ። ጥቅሶቹን እንመልከታቸው፤

1ኛ) ዮሐ. 14፥15-16 እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ #አጽናኝ ይሰጣችኋል፤ እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለ ሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፤ ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ።

ይህንን ጥቅስ ለሙሐመድ የሚጠቅሱ ከሆኑ፥ ሀ) ወልድ አብን እንደሚለምን፥ ለ) ከእነርሱ ከሐዋርያቱ ጀምሮ ከደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ጋር የሚኖር አጽናኝ እንደሚሰጣቸው፥ ሐ) ዓለም እንደማያውቀውና እንደማይቀበለው፥ መ) መንፈስ እንደሆነ፥ ሠ) በእነርሱ ዘንድ ብቻ ሳይሆን በውስጣቸውም እንደሚኖር ተነግሮአል። ሙሐመድ እነዚህን ሁሉ ያሟላል? ልብ እንበል በሐዋርያቱ ውስጥ ነው የሚኖረው። ሐዋርያቱ ሙሐመድ ተወልዶ በውስጣቸው እስኪገባ ኖረዋል ወይም ሙሐመድ ከመወለዱ በ500 በላይ ዓመታት በፊትም ነበረ ማለት ነው።

2ኛ) ዮሐ. 4፥26 አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው #አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል።

ይህንን ጥቅስ ለሙሐመድ የሚጠቅሱ ከሆኑ፥ ሀ) የሚልከው አብ መሆኑን፥ ለ) የሚላከው በኢየሱስ ስም መሆኑን፥ ሐ) ሁሉን እንደሚያስተምር፥ መ) ኢየሱስ የነገራቸውን እንደሚያሳስብ፥ ሠ) አጽናኙ በግልጽ መንፈስ ቅዱስ እንደተባለ ይቀበላሉ ማለት ነው?

3ኛ) ዮሐ. 15፥26 ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ #አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ፥ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል፤

ይህንን ጥቅስ ለሙሐመድ የሚጠቅሱ ከሆኑ፥ ሀ) አጽናኙን ከአብ ዘንድ የሚልከው ኢየሱስ መሆኑን፥ ለ) ከአብ የሚወጣ መሆኑን፥ ሐ) ስለ ኢየሱስ እንደሚመሰክር ይቀበላሉ ማለት ነው? ሙሐመድን የላከው ኢየሱስ መሆኑን ይቀበላሉ ማለት ነው?

4ኛ) እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ፤ እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል። እኔ ባልሄድ #አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና፤ እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ።

ይህንን ጥቅስ ለሙሐመድ የሚጠቅሱ ከሆኑ፥ ሀ) ኢየሱስ ሲሄድ ብቻ አጽናኙ እንደሚመጣ፥ ለ) ኢየሱስ እርሱን እንደሚልከው ይናገራል። ኢየሱስ አጽናኙን ሙሐመድን እንደላከው ይቀበላሉ ማለት ነው?

የነ አሕመድ ዲዳት ፔሪክሉቶስ ገደል ገባ!!

# ፈጽሞ ያማረው ሙሐመድ

ሦስት፤

*ፈጽሞ ያማረው ሙሐመድ*

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሙሐመድ ተተንብዮአል የሚሉትን ሙሐመድ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለማግኘት ሙስሊሞች የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም። ቀደም ሲል ሁለቱን፥ ‘የሙሴ ወንድም ሙሐመድ’ እና ‘አጽናኙ ሙሐመድ’ በሚሉ ርእሶች ሁለት ስለ ሙሐመድ የተነበሩ ምንባቦች ናቸው የሚሏቸውን ተመልክተናል።

ሙስሊሞች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥቅስና ምንባብብ ለመፈንቀል የሚለፉት የኢስላም ነቢይ ሙሐመድ በተውራት (ኦሪት ወይም ብሉይ ኪዳን) እና ኢንጅል (ወንጌል ወይም አዲስ ኪዳን) ማለትም፥ በአይሁድ እና በክርስቲያኖች መጽሐፍ፥ ተደጋግሞ እንደተጻፈና እንደተተነበየ ስለሚመስላቸው ነው። ይህን የሚሉት በሱራ 61፥6 ዒሳ ከእርሱ በኋላ አሕመድ የተባለ መልእክተኛ እንደሚመጣ ስለ ተናገረ ነው። ጥቅሱ እንዲህ ይላል፤

የመርየም ልጅ ዒሳም፡- «የእስራኤል ልጆች ሆይ! እኔ ከተውራት በፊቴ ያለውን የማረጋግጥና ከእኔ በኋላ በሚመጣው መልክተኛ ስሙ አሕመድ በኾነው የማበስር

ስኾን ወደእናንተ (የተላክሁ) የአላህ መልክተኛ ነኝ» ባለ ጊዜ (አስታውስ)፡፡ በግልጽ ተዓምራቶች በመጣቸውም ጊዜ «ይህ ግልጽ ድግምት ነው» አሉ፡፡ ይላል።

ዛሬ የምንመለከተው ያማረው ሙሐመድን ነው። ይህ ስለ ሙሐመድ ተነገረ የሚሉት ክፍል በመኃ. 5፥16 የሚገኘው ነው፤ በአማርኛው ትርጉም ይህ ነው።

አፉ እጅግ ጣፋጭ ነው፥ እርሱም ፈጽሞ ያማረ ነው፤ እናንተ የኢየሩሳሌም ቈነጃጅት ሆይ፥ ውዴ ይህ ነው፥ ባልንጀራዬም ይህ ነው።

ዕብራይስጥ ወደ ከቀኝ ወደ ግራ ነው የሚነበበውና አማርኛውንም ከቀኝ ወደ ግራ ስናነብበው እንዲህ ነው።

16 חִכּוֹ מַמְתַקִּים וְכֻלּוֹ מַחֲמַדִּים זֶה דוֹדִי וְזֶה רֵעִי בְּנוֹת יְרוּשָׁלִָם׃

የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት ባልንጀራዬ ይህ (ነው) ወዳጄ ይህ ያማረ ሁለመናው የሚጣፍጥ አፉ

ወደ ግራ የተጻፈውን ከግራ ወደ ቀኝ ስንመልሰው፥ አፉ የሚጣፍጥ፥ ሁለመናው ያማረ (ነው)፤ ወዳጄ ይህ፥ ባልንጀራዬም ይህ (ነው)፤ እናንተ የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት (ሆይ)።

የተፈለገው ቃል ያማረ የሚለው ነው። በዕብራይስጥ מַחֲמַדִּים (ማኽማዲይም) ሲሆን ምንጩ מַחְמָד (ማኽማድ) ነው። ማኽማዲይም ሲበዛ ወይም ሲጋነን ነው። ሲጋነን የሚለውን ኢም ወይም ኢይም (ማኻማዲይም) አሳብ ሙስሊሞች የአክብሮት አጠራር ነው ብለውም ይከራከራሉ። የዕብራይስጥ አጻጻፍና አነጋገር እንዲህ ያለውን አጠራር በመጠቀም ለነገሮች አክብሮት አይጠቀምበትም። ዐውዱን እና ማን ስለ ማን እየተናገረ እንደሆነ እናቆየውና ቃሉን እንደ ቃል ብቻ እንውሰደው።

ማኽማድ የዕብራይስጥ ቃል ነው፤ አንድ ነገርን ገላጭ ቅጽል ነው፤ ስምም አይደለም። ቃሉ እንደ ቅጽል ከዚህ ከመኃልየ መኃልይ ሌላ 12 ጊዜያት ተጽፎ ይገኛል። እንድትመለከቷቸው ጥቅሶቹ እነዚህ ናቸው፤ 1ነገ. 22፥6፤ 2ዜና 36፥19፤ ኢሳ. 64፥11፤ ሰቆ. 1፥10 እና 11፤ 2፥4፤ ሕዝ. 24፥16፥21 እና 25፤ ሆሴ. 9፥6 እና 16፤ ኢዩ. 3፥5 ናቸው። በነዚህ ጥቅሶች፥ ማኽማድ ወይም ማኽማዲይም የተባሉት ቃላት፥ ደስ የሚያሰኝ፥ መልካም፥ ያማረ፥ የከበረ፥ የሚያምር፥ አምሮት፥ ጌጥ፥ ፍሬ የሚሉ ናቸው። አንዳንዶቹ እንደ ስም ቢመስሉም በተጠቀሱባቸው ቦታዎች ሁሉ እንደ ቅጽል ነው የተጠቀሱት።

ይህ ቃል የመነጨበት ግስም አለው፤ חָמַד (ኻማድ) ይሰኛል። መደሰት፥ ደስ መሰኘት፥ መውደድ፥ መመኘት ማለት ነው። እዚሁ መኃ. 2፥3 ወድጄ ተቀመጥሁ በሚለው ወድጄ የሚለው ያ ግስ ነው። ዘፍ. 2፥9፤ ደስ የሚያሰኝ፥ ዘጸ. 20፥17፤ ዘዳ፣ 7፥25፤ አትመኝ፥ መዝ. 68፥16፤ ወደደው፥ ወዘተ፥ የሚለው ይህ ግስ ነው።

ስለዚህ፥ ማኽማድ ወይም ማኽማዲይም የተለመደ የዕብራይስጥ ቃል ነው። የሰው ስም አይደለም፤ ከተጠቀሰባቸው ቦታዎች በአንዱም እንኳ የሰው ስም ሆኖ አልተጠቀሰም። እንዲያው ነው ብለን ብንወስድ እንኳ ሙሐመድ ከሚለው ስም ጋር በድምጸት (phoneticism) ተቀራረበ እንጂ በዕብራይስጥ ካለው የቃሉ ትርጉም ጋር አይሄድም። ሙሐመድ ሀምድ ከሚል ቃል የመነጨ ሆኖ የተከበረ ማለት ነው። ይህኛው ደግሞ ከክብር ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው የማማር ጉዳይ ነው። ብሉት ኪዳን በአማርኛ የተጻፈ ቢሆን ኖሮ ከዚህ ቃል ስም ብናወጣ፥ መልካሙ ወይም አማረ ነበር የሚፈጠረው ስም የሚሆነው።

ይህ እንግዲህ ዐውዱን ሳንነካ ነው። ወደ ዐውዱ ስንመለስ መኃልየ መኃልይ በሁለት ፍቅረኞች መካከል የተደረገ ተውኔታዊ ንግግር ነው። ሦስተኞችም፥ የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት የተባሉ አሉ። አንዳቸው ለሌላቸው ያላቸውን የጋለ ፍቅር የሚገልጡበት መጽሐፍ ውስጥ ይህቺን ጥቅስና በውስጧ የሚገኝ አንድ ቃልን አውጥቶ ይህ ስለ ሙሐመድ የተነገረ ነው ማለት መጽሐፍ ቅዱስን ከቶም አለማወቅ ነው። ለነገሩ እንዲህ የሚሉ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን አያውቁትምም፤ አይቀበሉትምም። ቢያውቁም ጥራዝ ነጠቅ እውቀት ብቻ ነው። ጥቅስ መርጠው ግን ሊወስዱ ይሞክራሉ።

ሌላው የዚህ ጥቅስ አወሳሰድ ችግር፥ ሙስሊሞች ለሙሐመድ ብለው የሚወስዱት ይህንን ብቻ ጥቅስ ነው? ወይስ ሌሎቹንም ማኽማድ እና ማኽማዲይም ያሉበትን ጥቅሶች በሙሉ ነው? ከሆነ ሙሐመድን የቤት ዕቃ፥ ጌጥ፥ የመቅደስ ዕቃ፥ ቤተ መቅደስ፥ የነቢዩ ሕዝቅኤል ሚስት፥ ወዘተ ሊያደርጉት ነው።

ስማችን ወይም ለስማችን የሚቀርብ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተገኘ ማለት መጽሐፍ ቅዱስ ስለኛ ተናገረ ማለት አይደለም። ዘላለም የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከ500 ጊዜ በላይ ተጽፏልና፥ 'ኢሳይያስ እኔን እያሰበ ነው የጻፈው፤ ሰሎሞንም ስለ እኔ ነው የተናገረው፤' ብል መቀወሴን ማረጋገጫ ነው።

# ማንበብ የማያውቀው ሙሐመድ

አራት፤

ማንበብ የማያውቀው ሙሐመድ

ሙስሊሞች የአይሁድና የክርስቲያኖች መጽሐፍ ስለ ኢስላም ነቢይ ስለ ሙሐመድ ትንቢቶች እንደተናገረና እነዚህ ትንቢቶች በተውራት (ኦሪት ወይም ብሉይ ኪዳን) እና ኢንጅል (ወንጌል ወይም አዲስ ኪዳን) ማለትም፥ በጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ (በአይሁድና በክርስቲያኖች መጽሐፍ) እንደሚገኙ ለማስረዳት ይሞክራሉ። ሙስሊሞች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥቅስና ምንባብ ለመፈንቀል የሚለፉት ልፋት ቀላል አይደለም። ይህን የሚሉት በሱራ 61፥6 ዒሳ ከእርሱ በኋላ አሕመድ የተባለ መልእክተኛ እንደሚመጣ ስለ ተናገረ ነው። ዒሳና ኢየሱስ ከቶም አንድ አይደሉም። ጥቅሱ እንዲህ ይላል፤

የመርየም ልጅ ዒሳም፡- «የእስራኤል ልጆች ሆይ! እኔ ከተውራት በፊቴ ያለውን የማረጋግጥና ከእኔ በኋላ በሚመጣው መልክተኛ ስሙ አሕመድ በኾነው የማበስር ስኾን ወደእናንተ (የተላክሁ) የአላህ መልክተኛ ነኝ» ባለ ጊዜ (አስታውስ)፡፡ በግልጽ ተዓምራቶች በመጣቸውም ጊዜ «ይህ ግልጽ ድግምት ነው» አሉ፡፡ ይላል።

ቀደም ሲል ሦስቱን፥ 'ሙሐመድ ተጠቀሰበት' የሚሉባቸውን ጥቅሶች ተመልክተናል። ይህ አራተኛው ነው። ይህ ከኢሳ. 29፥12 የተወሰደው፥ 'ደግሞም መጽሐፉን ማንበብን ለማያውቅ፡- ይህን አንብብ ብለው በሰጡት ጊዜ እርሱ፡- ማንበብ አላውቅም ይላቸዋል።' የሚለው ነው። ይህንን ጥቅስ ሙሐመድ ማንበብና መጻፍ የሚችል ሰው አይደለምና ስለ እርሱ የተነገረ ቃል ነው ይላሉ።

ሙስሊሞች ጥቅስን ነጥለው ሲያወጡ ዋናውን አሳብ ይሸፍናሉና ይህን ክፍል በስፍራውና በዐውዱ እስኪ እንመልከተው። አሳቡን ለመረዳት ጠቅላላውን የኢሳይያስን መጽሐፍና ቢያንስ ደግሞ ጠቅላላውን ምዕራፍ መመልከት አስፈላጊ ቢሆንም፥ ያንን ማድረግ ሰፊ ስለሆነ የጥቅሱን የቅርብ ዐውድ ብቻ (ኢሳ. 29፥9-16) እንይ።

9 ተደነቁ ደንግጡም፤ ተጨፈኑም ዕውሮችም ሁኑ፤ በወይን ጠጅ አይሁን እንጂ ሰከሩ፤ በሚያሰክር መጠጥ አይሁን እንጂ ተንገደገዱ። 10 እግዚአብሔር የእንቅልፍ መንፈስ አፍስሶባችኋል ዓይኖቻችሁን ነቢያትንም ጨፍኖባችኋል ራሶቻችሁን ባለ ራእዮችን ሸፍኖባችኋል። 11 ራእዩም ሁሉ እንደ ታተመ መጽሐፍ ቃል ሆኖባችኋል፤ ማንበብንም ለሚያውቅ፡- ይህን አንብብ ብለው በሰጡት ጊዜ እርሱ፡- ታትሞአልና አልችልም ይላቸዋል፤ 12 ደግሞም መጽሐፉን ማንበብን ለማያውቅ፡- ይህን አንብብ ብለው በሰጡት ጊዜ እርሱ፡- ማንበብ አላውቅም ይላቸዋል። 13 ጌታም፡- ይህ ሕዝብ በአፉ ወደ እኔ ይቀርባልና፥ በከንፈሮቹም ያከብረኛልና፥ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነውና፥ በሰዎች ሥርዓትና ትምህርት ብቻ ይፈራኛልና 14 ስለዚህ፥ እነሆ፥ ድንቅ ነገርን በዚህ ሕዝብ መካከል፥ ድንቅ ነገርን ተአምራትንም፥ እንደ ገና አደርጋለሁ፤ የጥበበኞችም ጥበብ ትጠፋለች፥ የአስተዋዮችም ማስተዋል ትሰወራለች። 15 ምክራቸውን ጥልቅ አድርገው ከእግዚአብሔር ለሚሰውሩ፥ ሥራቸውንም በጨለማ ውስጥ አድርገው፡- ማን ያየናል? ወይስ ማን ያውቀናል? ለሚሉ ወዮላቸው! 16 ይህ የእናንተ ጠማምነት ነው፤ እንደ ሸክላ ሠሪ ጭቃ የምትቈጠሩ አይደላችሁምን? በውኑ ሥራ ሠሪውን፡- አልሠራኸኝም ይለዋልን? ወይስ የተደረገው አድራጊውን፡- አታስተውልም ይለዋልን?

እንግዲህ ቁጥር 12 ስለ ሙሐመድ ነው የተባለው ከዚህ ምንባብ እንደ ስንደዶ ተመዝዞ ነው። ክፍሉ ስለምን ይናገራል? ኢሳይያስን እነማንን ነው የሚናገረው?

አንደኛ፥ ሁለተኛ፥ ኢሳይያስ ከየትኞቹም ነቢያት የበለጠ ስለ መሢሑ የተነበየ ነቢይ ነው። ኢሳይያስን በዚህ ልክ ስለ ሙሐመድ ተነበየ ማለት ማቃለል ነው።

ሁለተኛ፥ ሙሐመድ አንብብ ተብሎ መጽሐፍ ሰጥተውት ነበር እንዴ? ይህን አንብብ ብለው በሰጡት ጊዜ እርሱ፡- ማንበብ አላውቅም ይላቸዋል። በሚለው ውስጥ ሰጪዎቹ በብዙ መደብ የተጻፉ ናቸው። ሰጪዎቹ ደግሞ ራሳቸው አይሁድ ናቸው። እንደ ቁርአን ደግሞ (96፥1-3) አንብብ ያለው ጅብሪል ነው። እንደ ሐዲሳቱ ደግሞ አንብብ ብቻ ሳይሆን፥ አንብብ ብሎ ጨምድዶ፥ ጨምቆ ይዞት ነው አንብብ ያለው። የመጀመሪያው ልዩነት እዚህ ላይ ነው። አይሁድ ለሙሐመድ መጽሐፍ አንብብ ብለው አልሰጡትም። እርሱም ማንበብ አላውቅም ብሎ አልመለሰላቸውም።

ሦስተኛ፥ ቀደም ሲል እንዳልኩት፥ ዐውድ የሚባል ነገር አለ። ኢሳይያስ ወዮታ ነው እየተናገረ ያለው። ኢሳ. 29ን ከመጀመሪያው አንሥተን ስናየው፥ ይሁዳና ኢየሩሳሌም ከእግዚአብሔር በመራቃቸው ምክንያት ቅጣት እየመጣባቸው ነው። ኢሳይያስ ትንቢትን የተናገረው ለአርኤል ወይም ዳዊት ለሰፈረባት አርኤል ነው። በዚህ ክፍል

አርኤል የኢየሩሳሌም ምሳሌያዊ ስም ነው። ስለ ኢየሩሳሌም የተነገረ ትንቢት ነው። ኢሳይያስ ይህን ከተናገረ ከወራት በኋላ ነው ሰናክሬም መጥቶ ይሁዳን የወጋውና ኢየሩሳሌንም የከበበው።

ይህ የሰናክሬም አደጋ እየመጣባቸው ግን የይሁዳ ሰዎች እንቢተኝነትና እንቅልፍና መፍዘዝ ላይ ናቸው። ይህን እንቢተኝነትና መፍዘዝ ነው ኢሳይያስ እየተናገረ ያለው። የይሁዳ ሰዎች እግዚአብሔር ደጋግሞ ቢናገራቸውም ከቶም የሚሰሙ አልሆኑም። ይህንን አንገተ ደንዳንነታቸውን እየገለጠ ነው። የተማረውን፥ 'አንብብ' ቢሉት፥ 'የታተመ ነው አላነብብም' ይላል፤ ያልተማረውን ቃሉ ይህ ነው አንብብ ቢባል፥ 'አልችልም' ይላል። የተማሩትም ያልተማሩትም ላለመታዘዝ፥ ቃሉን የተጻፈውን፥ ቀድሞ የተነገራቸውን ቃል ላለማንበብ፥ ላለመስማት፥ ላለመታዘዝ ሰበበኞች ናቸው። ቃሉን አይፈልጉትም፤ መታዘዝንም አይፈልጉም። በከንፈራቸው ያመልኩታል፤ ልባቸው ግን ከእርሱ የራቀ ነው። ይህንን ባለመፈለጋቸው ነው ከቁ. 14-16 የተጻፈው ቅጣት እየመጣባቸው ያለው።

ይህንን ነው ኢሳይያስ ለሕዝቡ እየተናገረ ያለው እንጂ ሙሐመድ ስለሚባል፥ እርሱ ትንቢት ከተናገረለት መሢሕ በኋላ 600 ዓመታት ቆይቶ በቁረይሾች መካከል ስለሚነሳ ሰው አይደለም። የአይሁድ መጽሐፍ አይሁድ ላልሆነው ለሙሐመድ የሚሰጥበት ምንም ምክንያት የለም። በትንቢተ ኢሳይያስ ወይም በጠቅላላው በመጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ ስለ ሙሐመድ የተነገረ ምንም ትንቢት የለም። አንድም!




አምስት፤

የአይሁድ ነቢይ ሙሐመድ

ባለፉት አራት ክፍሎች ሙስሊሞች በአይሁድና በክርስቲያኖች መጽሐፍ፥ በተውራት (ኦሪት ወይም ብሉይ ኪዳን) እና ኢንጅል (ወንጌል ወይም አዲስ ኪዳን) ማለትም፥ በጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ (በአይሁድና በክርስቲያኖች መጽሐፍ) ስለ ኢስላም ነቢይ ስለ ሙሐመድ ትንቢቶች እንደተጻፉና እነዚህ ትንቢቶችም ወደ ሙሐመድ አመልካች እንደሆኑ የሚናገሩባቸውን አራት ምንባባት ተመልክተናል። ይህ አምስተኛውና የመጨረሻው ነው።

ሙስሊሞች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥቅስና ምንባብ በመፈንቀል ወደ ሙሐመድ ለማመልከት የአመልካቹን ቀስት አቅጣጫ ለመጠምዘዝ የሚለፉት በሱራ 61፥6 ዒሳ ከእርሱ በኋላ አሕመድ የተባለ መልእክተኛ እንደሚመጣ ዒሳ ስለ ተናገረ ነው። ጥቅሱ እንዲህ ይላል፤

የመርየም ልጅ ዒሳም፡- «የእስራኤል ልጆች ሆይ! እኔ ከተውራት በፊቴ ያለውን የማረጋግጥና ከእኔ በኋላ በሚመጣው መልክተኛ ስሙ አሕመድ በኾነው የማበስር ስኾን ወደእናንተ (የተላክሁ) የአላህ መልክተኛ ነኝ» ባለ ጊዜ (አስታውስ)፡፡ በግልጽ ተዓምራቶች በመጣቸውም ጊዜ «ይህ ግልጽ ድግምት ነው» አሉ፡፡ ይላል።

ይህ የቁርኣኑ ዒሳ የተናገረው ነው። የቁርኣኑ ዒሳና የመጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስ ከቶም አንድ አይደሉም። በዚህ ጉዳይ ራሱን የቻለ መጽሐፍ ጽፌአለሁና እዚህ ተመልከቱት፤ https://t.me/zelalemmengistu/462

ቀደም ባሉት ክፍሎች አራት 'ሙሐመድ ተጠቀሰበት' የሚሉባቸውን ምንባቦችን ተመልከተናል። ይህ አምስተኛውና የመጨረሻው ነው። አይሁድ መጥምቁ ዮሐንስን ማን መሆኑን ጠይቀውት ነበር። ጥያቄውን በስፍራው በክፍሉ እንድመለከተው የጥያቄውን ጥቅስ ብቻ ሳይሆን አብረውት ያሉትኝ ጥቅሶችም ጨምሬ ልጻፍ፤ ዮሐ. 1፥19-27

19 አይሁድም፡- አንተ ማን ነህ? ብለው ይጠይቁት ዘንድ ከኢየሩሳሌም ካህናትንና ሌዋውያንን በላኩበት ጊዜ፥ የዮሐንስ ምስክርነት ይህ ነው። 20 መሰከረም አልካደምም፤ እኔ ክርስቶስ አይደለሁም ብሎ መሰከረ። 21 እንኪያስ ማን ነህ? ኤልያስ ነህን? ብለው ጠየቁት። አይደለሁም አለ። ነቢዩ ነህን? አይደለሁም ብሎ መለሰ። 22 እንኪያስ፡- ማን ነህ? ለላኩን መልስ እንድንሰጥ፤ ስለራስህ ምን ትላለህ? አሉት። 23 እርሱም፡- ነቢዩ ኢሳይያስ እንዳለ፡- የጌታን መንገድ አቅኑ ብሎ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ እኔ ነኝ አለ። 24-25 የተላኩትም ከፈሪሳውያን ነበሩና፡- እንኪያስ አንተ ክርስቶስ ወይም ኤልያስ ወይም ነቢዩ ካይደለህ፥ ስለ ምን ታጠምቃለህ? ብለው ጠየቁት። 26 ዮሐንስ መልሶ፡- እኔ በውኃ አጠምቃለሁ፤ ዳሩ ግን እናንተ የማታውቁት በመካከላችሁ ቆሞአል፤ 27 እኔ የጫማውን ጠፍር ልፈታ የማይገባኝ፥ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ ይልቅ የሚከብር ይህ ነው አላቸው።

ምንባቡ ይህ ነው። ጥያቄው ቁጥር 21 ላይ የሚገኘው፥ 'እንኪያስ ማን ነህ? መሢሑ ነህን?' አይደለሁም አለ። ኤልያስ ነህን? ብለው ጠየቁት። አይደለሁም ብሎ መለሰ። ነቢዩ ነህን? አይደለሁም አለ። የሚለው ነው። ከአይሁድ ጥያቄ የምንመለከተው አይሁድ መሢሕን፥ ኤልያስን፥ ነቢይን ይጠብቃሉ። ሦስት ጠቅሰው ነው እነዚህን ነህ ወይ ያሉት። መሢሕ፥ ኤልያስ፥ ነቢይ። አይሁድ ስለማንነቱ ብቻ ሳይሆን ለምን እንደሚያጠምቅም ነው የጠየቁት። 'አንተ መሢሑ ካልሆንክ፥ የሚመጣውም ነቢይ ወይም ኤልያስ ካልሆንክ፥ ወይም ነቢዩ ካልሆንክ ለምን ታጠምቃለህ? ነው ጥያቄያቸው።

የሙስሊሞች ሙግት፥ 'እንደሚጠበቅ የተነገረ ነቢይ አለና ያ ነቢይ እስከ ኢየሱስ ዘመን ድረስም ያልመጣ ነቢይ ነውና ሙሐመድ ነው።' የሚል ነው። እውነት ነው? እውነት ሙሐመድ በመጽሐፍ ቅዱስ ተተንብዮአል? ሦስት ነጥቦችን እንመልከት።

1ኛ) ዮሐንስ መሢሑን አለመሆኑን ራሱ መመስከር ብቻ ሳይሆን ከእርሱ በኋላ እንደሚመጣና በመካከላቸው የሚገኝ አንድ መኖሩንም አብሥሮአል። ይህ መሢሕ መሢሕ ብቻ ሳይሆን የሚጠብቁት ነቢይም መሆኑን ቀደም በክፍል አንድ ስለ ሙሴ የተነገረውን ምንባብ ስንመለከት አይተናል። ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ እንደሚያስነሣላቸው ተነግሮአቸው ነበርና ያንን ይጠብቁ ነበር። የዚያን ፍጻሜም ተመልክተናል። ያ ነቢይ ሙሐመድ ሳይሆን ኢየሱስ መሆኑን በክፍሉ በዝርዝር አመልክቼአለሁና በዚያ ተመልከቱት።

2ኛ) አይሁድ መሢሑ ከመምጣቱ በፊት ኤልያስ እንደሚመጣ ትንቢት ተነግሮላቸዋል፤ ይህንን በሚል. 4፥5-6 እነሆ፥ ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ ነቢዩን ኤልያስን እልክላችኋለሁ። መጥቼም ምድርን በእርግማን እንዳልመታ እርሱ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች፥ የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች ይመልሳል። ተብሎ ተጽፎአል። ኋላ ከጌታ ትምህርት እንደምንረዳው ደግሞ፥ በኤልያስ የተሰየመው የመሢሑ መንገድ ጠራጊ መጥምቁ ዮሐንስ ነው።

ደቀ መዛሙርቱም፦ እንግዲህ ጻፎች፦ ኤልያስ አስቀድሞ ሊመጣ ይገባዋል ስለ ምን ይላሉ? ብለው ጠየቁት። ኢየሱስም መልሶ፦ ኤልያስማ አስቀድሞ ይመጣል ሁሉንም ያቀናል፤ ነገር ግን እላችኋለሁ፥ ኤልያስ ከዚህ በፊት መጣ፤ የወደዱትንም ሁሉ አደረጉበት እንጂ አላወቁትም፤ እንዲሁም ደግሞ የሰው ልጅ ከእነርሱ መከራ ይቀበል ዘንድ አለው አላቸው። ማቴ. 17፥10-12

3ኛ) ልብ እንበል፤ የሚጠብቁት አይሁድ ናቸው እንጂ ሌሎች ሕዝቦች አይደሉም። ደግሞም ተስፋው የተሰጠው ለአይሁድ ነው እንጂ ለሌላ ሕዝብ አይደለም። እንዲያው ይሁን እንበል፤ ነቢዩ ገና ይመጣልም እንበል፤ ግን በምን ሂሳብ ተሰልቶ ነው ለአይሁድ ይመጣል የተባለው ነቢይ አይሁድን ትቶ በሙሐመድ ተከስቶ ለቁረይሽ ዐረቦች የተላከው? ይመጣል የተባለው.. እልክላችኋለሁ የተባለው ለአይሁድ አይደለም እንዴ? ከኢየሱስ መምጣት ከ600 ዓመታት በኋላ እይሁድ ወደ ቁረይሽ ተለወጡ?

በቁርኣን ደግሞ ወደ ሕዝቦች የሚሄድ ነቢይ የራሳቸውን ቋንቋ ተናገሪ መሆኑ ዋናው መስፈርት ነው። የሚከተሉትን የቁርኣን ጥቅሶች ተመልከቱ፤

ከመልክተኛ ማንኛውንም፤ ለነርሱ ያብራራላቸው ዘንድ በወገኖቹ ቋንቋ እንጂ በሌላ አልላክንም፤ አላህም የሚሻውን ያጠማል፤ የሚሻውንም ያቀናል፤ እርሱም አሸናፊው ጥበበኛው ነው። (14፥4)

በአዕጀምኛ የሆነ ቁርአን ባደረግነው ኖሮ (በምናውቀው ቋንቋ) አይብራሩም ኖሯልን? (ቁርአኑ) አዕጀምኛና (መልክተኛው) ዐረባዊ ይሆናልን? ባሉ ነበር፤ እርሱ ለነዚያ ለአመኑት መምሪያና መፈወሻ ነው። እነዚያም የማያምኑት በጆሮዎቻቸው ውስጥ ድንቁርና ነው፤ (አይሰሙትም) እርሱም በነርሱ ላይ ዕውርነት ነው፤ እነዚያ ከሩቅ ስፍራ እንደሚጥጠሩ ናቸው። (41፥44)

(ቁር አኑን) በቋንቋህ ያገራነው፣ (ሕዝቦችህ) ይገነዘቡ ዘንድ ብቻ ነው። (44፥58)

ከበፊቱም የሙሳ መጽሐፍ መሪና ጸጋ ሲሆን አለ ይህም እነዚያን የበደሉትን ሊያስፈራራ በዐረብኛ ቋንቋ ሲሆን (የፊቶቹን መጻሕፍት) አረጋጋጭ መጽሐፍ ነው ለበጎ አድራጊዎችም ብስራት ነው። (46፥12)

ከላይ እንደተመለከትናቸውና ሌሎችም አንቀጾች ለየሕዝቡ በቋንቋቸው ነው ነቢይ የሚላክላቸው። ለአይሁድ አይሁዳዊ፥ ለዐረብ ዐረባዊ፥ ኤኢትዮጵያም ኢትዮጵያዊ ነው የሚላከው። የጃፓኑ ለቻይናው፥ የዐረቡ ለአይሁድ አይላክም። ሙሐመድ የተላከው ለቁረይሾች እንደሆነው ወደ አይሁድ የሚመጣው ነቢይም ከአይሁድ ነው እንጂ ከሌላ አይደለም። ይህ እንደ ቁርኣን ትምህርት ነው። ስለዚህ ይህንን የዮሐንስ 1፥21ን ጥቅስ፥ 'ስለ አይሁድ ሳይሆን ስለ ሌላ ነው' ብሎ አፈፍ ማድረግ እንዲችል ማንም መሞከር ቀርቶ ማሰብም የለበትም።

ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ስንመጣ ደግሞ ተስፋው የተሰጠው ለአይሁድ፥ ነቢዩም የሚመጣው ከአይሁድና ለአይሁድ ነው። ይህንን ምንባብ በምንም መንገድ ሙስሊሞች ስለ ሙሐመድ የተነገረ ነው ብለው ሊወስዱት አይችሉም። ሙሐመድ ለዕብራይስጥ ተናጋሪዎች አልተላከም። ሙሐመድ የአይሁድ ነቢይ አይደለም።

ዘላለም መንግሥቱ